# የፈረስ ልጅ ጥሎ ይደነግጣል፣ የአህያ ልጅ ጥሎ ይረግጣል

ከሲመሽ ተገኝ

መቼም በሃገራችን ላለፉት አርባና ሃምሳ ዓመታት ሲካሄድ በነበረውና አሁንም እየተካሄደ ባለው የፖለቲካ ውጣ ውረድ ምክንያት ብዙ ክስተቶችን ተመልክተናል። አይበገር ይመስለን የነበረው የንጉሡ የዘውድ አገዛዝ በወታደሮች ሲገረሰስ፣ በአፍሪካ ተመጣጣኝ የማይገኝለት የጦር ኃይል ተብሎ ይነገረን የነበረው የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት በሽፍቶች ተሸንፎ ያለጡረታ ተበትኖ በየመንገዱ ዳር ሜዳሊያውንና ኒሻኑን ደርድሮ ሲለምን፣ ሽፍቶች ቤተመንግሥት ገብተው ሲገዙ፣ የትናንት አሳሪዎችና ገራፊዎች ዛሬ በተራቸው ታሳሪና ተገራፊዎች ሆነው ብዙ ነገሮች ተለውጠውና ተገልብጠው ለማየት ዕድሜውን ሰጥቶናል።

ንጉሡን ከዙፋን ያወረዱት ኮሳሳና ከሲታ ወታደሮች ቤተ መንግሥቱንና ድሎቱን ተለማምደውት ደማቸው ከቆዳቸው ስር ሲሯሯጥ መታየት ሲጀምርና እብሪት ተጸናውቷቸው ከእኛ በላይ ለአሳር ነው ማለት ጀምረው በሕዝቡ ሲሳለቁና ሲያፌዙ ምሥክር ነበርን። ጤፍ ከከተማችን ጠፍቶ ሕዝቡ በቆሎ፣ ሩዝና ማሽላ እንዲበላ በቀበሌ በኩል ሲቀርብለት፣ አንዳንድ የመረጃ ሠራተኞች ሕዝቡ እነዚህን የእህል ዘሮች መብላት መልመድ እንዳስቸገረው ሪፖርት ሲያቀርቡ፣ የደርግ አባላት "እኛም ዊስኪውን መጠጣትና ጮማውን መቁረጥ በብዙ ችግር ነው የለመድነውና፣ ቀስ ብሎ ይለምደዋል" ብለው በሕዝቡ ረሃብ አፌዙበት እየተባለ ይወራ ነበር።

አሁንም ተረኞቹ ገዢዎች ከአስራ ስምንት ዓመታት በላይ በሥልጣን ላይ በመቆየታቸው፣ ልክ ከበፊታቸው እንደነበሩት ሹሞች ሁሉ፣ ከጊዜ በኋላ በመጣ ድሎት ወዛም ሆነውና ከቆዳቸው በታች ደማቸው ሲሯሯጥ መታየት ከጀመረ ዓመታት አስቆጠሩ። በዕርግጥ አንዳንዶቹ ለብዙ ዘመን ሲጓጉለት የነበሩትንና ተነፍገውት የነበረውን ምግብ፣ መጠጥ፣ ሲጋራና ጫት በገፍ በማግኘታቸው ሰቀቀን ሆኖባቸው ራሳቸውን ባለመቆጣጠራቸውና ከመጠን በላይ በማግበስበሳቸው የጤና መታወክና የከንፈር ኩበት መምሰል ቢታይባቸውም፣ ጌትነቱን እየለመዱት ነው። እንግዲህ በእንደዚህ ዓይነቱ የመንደላቀቅና የድሎት ወቅት ነው መሪዎች ተነሳንበት የሚሉትን ዓላማ ዘንግተው፣ በእብሪት ተወጥረው፣ ከሕዝብ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ተራርቀው፣ ከመሰሎቻቸው ጋር ብቻ በመገናኘት፣ ያለውን ዕውነታ ረስተው በራሳቸው የቅዠት ዓለም ውስጥ መኖር የሚጀምሩትና ሕዝብ እየተራበ እነሱና መሰሎቻቸው ጮማ በልተው ብስና ስላስቸገራቸው ሕዝቡ የጠገበ የሚመስላቸው፣ እነሱና ጥቂት አጫፋሪዎቻቸው ከቁምጣ ሱሪና ከአቧራ ላይ መኝታ ወጥተው ምርጥ ሱፍ መለዋወጥ በመጀመራቸውና ቤተ መንግሥትና ቪላ ውስጥ በመኖራቸው፣ የእነሱ ኑሮ በተሻሻለ፣ ኑሮው እንደ ጅራት ቁልቁል የሚያድገውን ሕዝብ ኑሮህ ተሻሽሏል ብለው ለራሱ ለተራበውና ለታረዘው ሕዝብ የሚነግሩትና፣ በተግባር

ኑሮውን የሚያውቀው ሕዝብ ግን ‘ልክ አይደላችሁም፣ እየተራብኩና እየታረዝኩ ነው’ ብሎ ሃቁን ሲነግራቸው በስድብ የሚያዋርዱትና በረሃቡና በእርዛቱ መቀለድ የሚጀምሩት።

የሚያስተዳድረውን ሕዝብ የሚንቅና የሚያዋርድ የሃገር መሪ ደግሞ፣ ከሌላ ሃገር የመጣ የቅኝ ገዥ እስካልሆነ ድረስ፣ ትልቅ ከፍታ ካለው ዛፍ ላይ ወጥቶ አንዱ ቅርንጫፍ ላይ ተቀምጦ፣ የተቀመጠበትን ቅርንጫፍ በመጋዝ እንደሚቆርጥ ጅል ነው የሚታየው። አንድ የሃገር መሪ የሚገዛውን ሕዝብ መናቅና ማዋረድ ሲጀምር የውድቀቱ መጀመሪያ አመላካች ነው። ይህንን የአምባ ገነኖች ባሕሪይ ስናይ ደግሞ የመጀመሪያ ጊዜያችን አይደለም፤ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምም ወደ መጨረሻው አካባቢ የኢትዮጵያን ሕዝብ እዚህ ላይ ለመድገም የሚያስፍር ስድብ ተሳድቦ ነበር። ያሁኑም በ99.6% የሕዝብ ድምጽ ተመረጥኩ የሚል መሪ ለአነጋገሩ ለከትና ሥርዓት የሌለውና ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ፣ ሃገሪቷንና ሕዝቧን የሚያዋርድ የሚሳደብና በሕዝቧ ረሃብና ችግር የሚያፌዝ ቧልተኛ ስለመሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

የነዳጅ ዋጋ በመጨመሩ ሕዝብ እንደሚቸገር ሲገለጽለት የታሸገ ውሃ አምስት ብር ገዝቶ የሚጠጣ ሕዝብ ነዳጅ ላይ በሳንቲም የሚቆጠር ዋጋ ተጨመረ ማለት እንደማይገባውና ሕዝብ ተቸግሯል ትላላችሁ ግን የልኳንዳ ቤቶች ቦታ ጠቧቸው ድንኳን ጥለው ነው በላተኛ የሚያስተናግዱትና ችግር የለም ብሎ የሚናገር ገዥ ነው ሃገሪቱ በአሁኑ ጊዜ ተሸክማ ያለችው። ለመለስ ዜናዊና ለአጫፋሪዎቹ፣ ሕዝብ ማለት እነዚህ የታሸገ ውሃ በአምስት ብር ገዝተው የሚጠጡትና በየቀኑ በየልኳንዳ ቤቱ እየዞሩ ብስል ከጥሬ ጮማ የሚቆርጡት የሱ ሹሞችና ጥቂት ሆዳሞች ናቸው እንጂ ሌላውማ ሕዝብ አይደለም። ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የታሸገ ውሃ የሚጠጣውና ጮማ የሚቆርጠው ሕዝብ ብዛት ስንት በመቶ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሊያስረዳን ይችል ይሆን? ወይስ ያው ቁጥር በማምታታት ካለው ልምድ ተነስቶ 99.6% ሕዝብ ነው በዚህ ሁኔታ በድሎት የሚኖረው ብሎ ይቀልድ ይሆን? የሃገር መሪዎች እንዲህ ማሾፍና በሕዝብ ቁስል ላይ ጨው መነስነስ ሲጀምሩ የመውደቂያቸው አዝማሚያ መሆኑ አያጠራጥርም። ከቀናው ያው እንደ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የዘረፈውን ዘርፎ አንዱ ሃገር ሄዶ በስደት ይኖራል፣ ያለበለዚያም ተይዞ ለፍርድ ይቀርባል ወይም አንዱ ብልጭ ያለበት ታጣቂ ይገድለውና የዘረፈውንና የደበቀውን ሃብት ሳይበላ ይቀራል።

መቼም ለጉድ የኀለተን ነን እና ያለፉትን ሁለት ‘ኃያል’ ብለን የገመትናቸውን መንግሥታት ውድቀት እንዳየነው ሁሉ፣ ያሁኑንም ራሱን ‘ዲሞክራሲያዊ፣ ሃገሪቱን በታሪኳ ታይቶ የማይታወቅ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ያደረስኩ’ እያለ የሚመጻደቅና ዘረኛ መንግሥት ውድቀት እንደምናይ አልጠራጠርም። ራሱን አሻሽሎ፣ የሚያወራውን ዲሞክራሲ ተግባራዊ አድርጎ፣ በሠላማዊ ምርጫ ሥልጣኑን ካላስረከበና ለውጥ በሌላ መልክ ከመጣ፣ የዛሬው ዕብሪተኛ ሹሞች

ሌሎች ተከሳሾች፣ ሌሎች ታሳሪዎችና ሌሎች ተመርማሪዎች ሆነው ይቀርባሉ። እናም በዚህ ጊዜ ነው የቂምና የበቀል እርምጃ ከመውሰድ መቆጠብ የጨዋና የበሰለ ሕዝብ መለኪያ የሚሆነው። የቂምና የበቀል እርምጃ አለመውሰድ ማለትም ተከሳሾችን በሕጋዊና በነጻ ፍርድ ቤት ጉዳያቸውን ተመልክቶ እንደየጥፋታቸው ተገቢውን ውሳኔ መስጠትና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ታሪካቸውን መዝግቦ ይቅር እስከማለት ድረስ መሄድ ነው።

በዕድሜያችን ባየናቸው ለውጦች ግን የዚህ ዓይነቱን ይቅር ባይነትና ፍትሕ ለማየት አልታደልንም። ደርግ ሥልጣን ላይ ሲወጣ ወታደራዊ ማርሽ ደልቆ ያለፍርድ የቀድሞ ባለሥልጣናትን ረሽኖ ከዚያም ለዓብዮት ጠባቂዎች፣ ለካድሬዎችና ለመርማሪዎች ጸረ ዓብዮተኛ ብለው በሚጠረጥሩት ላይ ነጻ እርምጃ ብለው እስከመረሸንና ሬሳቸውንም ለመቀጣጫ በየመንገዱ ዳር እስከመጣል ድረስ የሚያስችል መብት ሰጥቶ የሰው ልጆች ሬሳ ተገቢውን ክብር ተገፍፎ መፈክር ተለጥፎበት መንገድ ዳር ወድቆ እንዲቆይ ተደረገ። በጠመንጃ በመታገዝም ሆነ በማጭበርበር ሥልጣን የሚቆናጠጡ አምባገነኖች በአገዛዝ ዘመናቸው ሥልጣናቸውን መከታ አድርገው ብዙ በደልና ግፍ ስለሚፈጽሙ፣ ዘወትር የሚያሳስባቸውና የሚያባንናቸው ነገር ቢኖር የሥልጣን ዘመናቸው ተፈጽሞ በሥልጣናቸው ምክንያት ያገኙት የነበረውን ያለመከሰስና ያለመወቀስ መብት ተገፍፈው ለፍርድ መቅረባቸው ነው። በመሆኑም ዘወትር ያንን መብት ይዘው ለመቆየት ሲሉ በሥልጣን ኮርቻ ላይ የሙጥኝ ብለው እስከ ዕለተ ሞታቸው ወይም እስከ ዕለተ ስደታቸው ድረስ ለመቆየት ይፈልጋሉ። የሥልጣን ዘመናቸው እየረዘመ በሄደ ቁጥር ደግሞ በደላቸውና ግፋቸው እየገዘፈና ወንጀላቸውም እየተጠራቀመ ስለሚሄድ ከሥልጣን ሲወርዱ ምን እንደሚጠብቃቸው ስለሚያውቁ ነገሩ የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም ነውና በወንጀል ላይ ወንጀል በበደል ላይ በደል እየጨመሩ ፍጹም አምባገነኖች ይሆናሉ። እንዲያውም አልፈው ተርፈው ሃገሪቱን ካለእነሱ በስተቀር ሌላ ማንም መምራት እንደማይችል ያምኑና፣ እራሳቸውን የሃገሪቱ የዕድሜ ልክ መሪ ብለው እስከመሰየም ይደርሳሉ። ግን፣ ማንኛውም ነገር የጊዜው መርዘምና ማጠር ይለያይ እንደሆን ነው እንጂ፣ መጀመሪያ እንዳለው ሁሉ መጨረሻም ስለሚኖረው፣ አንድ የሚወድቁበት ቀን እንደሚመጣ ሐቅ ነውና ብዙ ነገሮች እየተዘነጉ ሊሄዱ ስለሚችሉ፣ ተከሳሾችም፣ ከሳሾችም፣ ምስክሮችም፣ ዳኞችምና ማስረጃዎች ጭምር ለዚች ጊዜ ተዘጋጅተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል። በተለይ ከበቀልና ከቂም የጸዱ ምስክሮች የሚፈለጉት በእንደዚህ ዓይነቱ የለውጥ ጊዜ ላይ ነው። አምነውበት ላደረጉት ተግባር ሲጠየቁ በወቅቱ አምኜበት ነበርና አድርጌዋለሁ ብለው የሚናገሩ ተከሳሾች አልፎ አልፎ እንዳየነው ሁሉ፣ ብዙ ወንጀለኞች ደግሞ የራሳቸውን ወንጀል ለመሸፋፈን ሲሉ ወንጀሉን ሁሉ ሸሽቶ በሄደው በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ላይ ሊለጥፉ ሲሞክሩ ተመልክተናል። ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ ምስክርነት ሲጠየቅ በምስክርነት የሚቀጠረው ሰው ማነው? ከከሳሹ ጋርስ ምን ዓይነት ቁርኝትና መተሳሰር አለው? ከተከሳሹስ ጋር ያለው ግንኙነት ምን ዓይነት ነው? በአጠቃላይስ ከዚህ ጉዳይ ምን የሚያገኘው ጥቅም አለ? የመሳሰሉት ጥያቄዎች ሁሉ መጤን አለባቸው። እንደዚህ ዓይነቶቹ ሁኔታዎች ሳይጤኑ ዝም ብለን ምሥክር ነኝ ብሎ የቀረበውን ግለሰብ

ምሥክርነት መቀበል የምንጀምር ከሆነ ግን በአንዳንድ የገጠር አካባቢ “አዳፍኔ” ተብለው እንደሚታወቁት በገንዘብና በጥቅም ተገዝተው የሚመሰክሩ የሓሰት ምስክሮችን በከፍተኛ ደረጃ ማበራከት ይሆናል።

ለዚህ ርዕስ መነሻ የሆነኝ በቅርቡ ያነበብኩት የተስፋዬ ርስቴ ‘ምስክርነት’ የተባለ መጽሐፍ ነው። ተስፋዬ ይህንን መጽሃፉን የደረሰው የቀድሞ የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ አስተዳደር አባል በመሆኑ፤ አዲስ በመጣው መንግሥት ታስሮ በነበረበት ጊዜ አብረውት ታስረው የነበሩትን የቀድሞ ባለሥልጣናት በማነጋገርና ቀደም ሲል በሥራ ላይ በነበረበት ዘመንም ካገኛቸው ሰነዶችና በምርመራም በቃለ ጉባዔ ጸሃፊነትም ከተሳተፈባቸው አንዳንድ ሥራዎች በመነሳት እንደሆነ ገልጿል። መቼም ስለደርግ የውስጥ አሠራር ከራሱ ከአባላቱና ከሾማቸው ሚንስትሮችና ሹማምንቶች አፍ ከመስማት የበለጠ ጥሩ ምንጭ አለ ለማለት አዳጋች ነው። ይሁንና ሻምበል ተስፋዬ ከመታሰሩ በፊት በሕዝብ ደህንንነት ውስጥ በመሥራቱ፤ ሲታሰርም የደርግን ባለሥልጣናት እንደልብ መገናኘት በመቻሉና በሙያውም የፖሊስ መኮንንና የሕግ ምሩቅ በመሆኑ ሚዛናዊ የታሪክ ምሥክርነት ያካተተ ጽሑፍ ያቀርባል በሚል ጉጉት ነበር መጽሐፉን ማንበብ የጀመርኩት። ሆኖም በመጽሐፉ ላይ ያሰፈረው አብዛኛው ይዘት በሰ ሙያም ሆነ የትምህርት ደረጃ ከሚገኙ ግለሰቦች የማይጠበቅ ሆኖ ነበር ያገኘሁት። አንኳር አንኳሮቹን ግድፈቶች በመጠኑም ቢሆን እጠቃቅሳለሁ።

## አድሎአዊነት

ሻ/ል ተስፋዬ በተለይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲን በተመለከተ ያለው አቋምና አመለካከት ደርግ በ1969 ዓም ካለው አመለካከትና ጥላቻ በፍጹም ያልተላቀቀና፤ የሚጠቀምባቸው ቃላትና ሓረጎች ሁሉ፤ በዚያን ዘመን የነበረው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የሚጠቀምባቸው ዓይነት ናቸው። ከመነሻው በጥላቻ ታውሮ የተነሳ ጸሃፊ በመሆኑ፤ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኢሕአፓን የሚወነጅልበት ምክንያት ሲያነፈንፍ ነው የሚታየው። ደራሲው ምንም እንኳን የማንም ወገን እንዳልሆነና ሚዛናዊ አስተያየት በመጽሐፉ ላይ እንደሚያሰፍር ቢገልጽም፤ በጽሁፍ ያሰፈረውን ቃል በውስጡ የተዳፈነው የጥላቻ ስሜት እያሸነፈበት፤ ገና ከመጽሐፉ መግቢያ ያለውን የጥላቻ መርዝ ሲረጭ ይገኛል። አንዳንዶቹን ለማመላከት ያህል፤

የንጉሡ ሥርዓት እንደወደቀ ስለነበረው የሦስት ቡድኖች የሥልጣን ሽሚያ ሻ/ል ተስፋዬ በመግቢያው ላይ ሲያቀርብ፤ መኢሶንን፤ ከሕብረተሰቡ መነጨን የሚሉት፤ ደርግን የመለዮ ለባሹ ቡድን ብሎ ሲያቀርብ ኢሕአፓን ግን ‘ቀይ ሸማ የለበሰው ኢሕአፓ (ሁኔታው ሲያጥጥ አብዛኞቹ የኢሕአፓ መሪዎች ከጡት እናታቸው አሜሪካ ነው የገቡት፤ እውነት ኮሚኒስት ቢሆኑማ እንዲያ አምርረው

*<u>ከሚጠሉት ደም መጣጭ ካፒታሊስት አገር ያውም አሜሪካ እንዴት ይሄዱ ነበር? ትክል ስለነበሩ ምዕራብ ገብተዋል።)</u>' መግቢያ ገጽ* VII (ስርዝ የተጨመረ)

*ገና መጽሃፉን ከፍቶ ሰባት ገጽ ብቻ ላነበበ ሰው ያሉትን የሥልጣን ተሻሚ ቡድኖች ስም መዘርዘር ብቻ ሲበቃ፣ ስለ ሌሎቹ ቡድኖች ምንም ሳይባል በአንዱ ቡድን ላይ ብቻ ያንን ያህል መተቸት እውን አንባቢውን ደራሲው ዕውነተኛና ሚዛናዊ አስተያየት ያሰፍራል ብሎ የሚያሳምን ይመስላል?*

*ሌላው መቼም ደራሲው ከጠቀሰው ዘንዳ አስተያየት መስጠት ያስፈልግ ይሆናልና ላንሳው እንጂ፣ ሻ/ል ለስሙ ደህንነት መሥሪያ ቤት ውስጥ ሠርቻለሁ ይላል፣ ግን ስለ ኢሚግሬሽን ያለው ግንዛቤ ከመኃይምናን ዘንድ የሚያስፈርጀው ሆኖ ነው ያገኘሁት። ወደ አንድ ሃገር ለመሰደድና ጥገኝነት ለመጠየቅኮ የፖለቲካ አመለካከት ብቻ ሳይሆን ብዙ አብረው የሚታዩ ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ የሚኬድበት ሃገር የኢሚግሬሽን ደንብ፣ ለጥቆ የአመልካቹ የግል ሁኔታዎችና ለሕይወቱና ለነጻነቱ የሚያሰጉት ሁኔታዎች ክብደት ሁሉ ሚዛን ውስጥ ገብተው ነው የሚወሰነው። እና ከእነዚያ ሁሉ የሥራ ባልደረቦችህ ከነበሩት የኢሠፓ አባላት፣ አምባሳደሮች፣ የኤምባሲ ሠራተኞች የነበሩ ባለቀይ ደብተር ኮሚዩኒስቶች መካከል እስቲ ማነው ኮሚዩኒስት ሃገር ሄዶ ጥገኝነት የጠየቀ? እንኳን ሌላ ቀርቶ በኮሚዩኒስት ሃገሮች አምባሳደሮች፣ ጸሃፊዎች፣ አታሼዎች የነበሩ የደርግ ባለሥልጣኖች ሳይቀሩ ወደ ምዕራቡ ሃገርና ወደ አሜሪካ ሄደው አይደለም ወይ ጥገኝነት የጠየቁት? እናስ እነዚያ ሁሉ ቱባ ኮሚዩኒስቶች አሜሪካ የገቡት የጡት አባታቸው አሜሪካ ሆኖ ነው? በየአደባባዩ ግራ እጃቸውን እያነሱ ካፒታሊዝም ይውደም ሲሉ የነበሩና ከእስር ያመለጡት፣ እንዳንተና እንደመሰሎችህ ሲንከረፈፉ ያልተያዙ ቀልጣፋ የደርግ አባላት፣ ለመሆኑ የት እንዳሉ ለማወቅ ጥረት አድርገሃል? መቼም አልሳካልህ ብሎ ነው እንጂ ከተሳካልህ አንተም አንድ ቀን መውጣትህ አይቀርምና ትምህርት ቢሆንህ፣ ሰዎች በስደት የሚሄዱበትን ሃገር የሚመርጡት ከሰብዓዊ መብቶቻቸው መከበርና ከሚሄዱበት ሃገር የኢሚግሬሽን ደንብ አንጻር እንጂ ኮሚዩኒስቶች ወደ ኮሚዩኒስት ሃገር ካፒታሊስቶች ወደ ካፒታሊስት ሃገር የሚል ደንብ እንደሌለ መገንዘቡ ይረዳል።*

*<u>የቃላት አመራረጥ</u>*

*በሥነ ጽሑፍ ላይ መቼም የቃላት አመራረጥ ታላቅ ሚና እንደሚጫወት የታወቀ ነው። ሴትዮዋ ምግብ ስታዘጋጅ አንድ ወዳጇ መጥታ 'ይህንን ምግብ ለማን ነው የምታዘጋጂው?' ብትላት፣ 'እሳቸው ከመጡም ይሰለቅጡታል፣ ከቀሩም እኔው እቀምሳታለሁ' ስትል ለእሷ ሲሆን አሳንሳ ለባሏ ሲሆን ግን አጋንና መለሰች የሚባለውን ዘይቤ ነው የሻ/ል ተስፋዬ አጻጻፍ በግልጽ የሚያሳየው።*

ተስፋዬ ሚዛናዊ አስተያየት ለመስጠት እንደሚፈልግ ሆኖ ቢቀርብም በኢሕአፓ ላይ ያለውን ጥላቻ ፊት ለፊት በማይገልጽበትም ጊዜ እንኳን በቃላት አመራረጡ ላይ ሳያውቀው ጥላቻው ይንጸባረቅበታል።

ስለ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጭካኔ በገጽ 73 ላይ ሲያወሳ፣ ከቃላት አመራረጡ እንኳን ማንን እንደሚደግፍና ማንን አጥብቆ እንደሚጠላ በግልጽ መረዳት ይቻላል።

> '...በመኢሶንና በምልስ የኢሕአፓ አባላት ተጠቅመው የኢሕአፓን ውስጣዊ አሠራር ተረድተው በእነርሱ መርማሪነትና ጭካኔ በብርቱ <u>መትተዋቸዋል</u>።' ይልና የወዝ ሊግን መመታት በዚያው ገጽ ላይ ሲያቀርብ ደግሞ 'በተለይም እነሻ ወልደ ማርያም ኃይሉን፣ ኮ/ል ሽታዬ ደስታን፣ ሻ/ ጌታቸው አግዴንና ሻ/ ብርሃኑ ከበደን <u>ሰውተዋል</u>' (ስርዝ የተጨመረ) ብሎ ያቀርበዋል።

በተስፋዬ አመለካከት የኢሕአፓ አባላት ሲገደሉ <u>መመታት</u> ሲሆን፣ እነ ሻ/ብርሃኑ ከበደን የመሰሉ የደርግ የምርመራ ክፍል ሹምና በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን አካለ ጎዶሎ ያደረጉና ገድለው የተጣሉበትን እንኳን ያላሳወቁ ሰዎች ሞት ለተስፋዬ <u>መስዋዕትነት</u> ነው። ይቺ ናት በቃላት ጨዋታ! የእነ ተኮላና የእነ ፈቃዱ ዋና አስተማሪ የነበረ አረመኔ መርማሪ፣ እነመንግሥቱን ፈንቅሎ ሥልጣን ሊይዝ የነበረ ቡድን አባል ሆኖ በመገኘቱ ተይዞ ሲገደል <u>ተሰዋ</u> ብሎ የሚገልጸው ተስፋዬ አድሎአዊ አይደለሁም ብሎ ሲናገር ማን ያምነኛል ብሎ ይሆን?

ይህንን የቃላት አመራረጥ ተስፋዬ በመኢሶን አባላት ላይ ስለተወሰደው እርምጃና መኢሶኖች ከደርግ አባላት ጋር ሆነው የፈጸሙትን ወንጀል ሲገልጽም፣ ድርጊቱን ለማግዘፍ በደንብ ተጠቅሞበታል። በመጽሐፉ ገጽ 119 ላይ ስለመኢሶን መሪዎች መያዝ ሲገልጽ 'ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ተቀምጦ በነበረው ልዩ ብሪጌድ ጦር እንደዶሮ እየተያዙ አንገታቸው ተቆልምሞ አልፈዋል' ሲል ያቀርበዋል። በዚሁ ገጽ ላይ ስለመኢሶኖች ወንጀል ሲያቀርብም 'የደርግና የመኢሶን አባላት እስር ቤት የታሰሩትን በሰከሩ ጊዜ እያወጡ የተኩስ መለማመጃ ያደርጓቸው የነበረውን ሕሊና ሲያስታውስ እጅግ የሚዘገንን ነው፡' ሲል ነው የሚያቀርበው። የሚያስደንቀው ነገር ሻ/ል ተስፋዬ አንድም ቦታ የኢሕአፓ አባላት ናቸው ተብለው በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ መርማሪዎችም ሆኑ የደርግ አባላት የወሰዱትን የጭካኔ ተግባር ሳያወግዝ፣ በዚህ ገጽ ላይ ግን የመኢሶን አባላት በድርጊቱ አብረው የተካፈሉ በመሆናቸው የእነሱን ወንጀል ለማግዘፍ ሲል 'የሚዘገንን' ሲል አስቀምጦታል። አንድም ቦታ እነ ብርሃኑ ከበደ እነ ተኮላ እነ ፈቃዱ አስቻለውና ሌሎች መርማሪዎች ወጣቶችን በሽቦ እያነቁ ሲገድሉ ድርጊቱ 'የሚዘገንን' ተብሎ በተስፋዬ አልተገለጸም። ወይንስ አንዳንድ አስተያየት ሰጭዎች ተናገሩኝ ብሎ ደራሲው እንደገለጸው የፖሊሶችን ወንጀል እያለባበሰ ይሆን? የሚያሰኝ ነው።

## ሁኔታዎችን ከአንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከት

መቼም ጸሃፊዎች ታሪካቸው ተዓማኒነት እንዲያገኝ ራሳቸው ያዩትንና የሰሙትን ማስረጃ ማቅረብ አንዱ ዘዴ ሲሆን፤ ሻ/ል ተስፋዬም በተለይ የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይን ሥም በዘረኝነት ለማጉደፍ የተጠቀመበት ዘዴ ጸሃፊው በአባዲና ፖሊስ ኮሌጅ በነበረበት ዘመን ዶክተር ተስፋዬ የፊሎዞፊ አስተማሪው እንደነበርና፤ ከክፍል ሲወጣ ገብረ ሥላሴ ዘድንግል፤ ኪዳነ ተስፋዬንና መሰለ ሐጎስን ለብቻቸው ጠርቶ ሳያነጋግር አይመለስም (ገጽ 101) በማለት ነው። የተስፋዬ ርስቴ አመለካከት በጥላቻ የታወረና እንደ ጋሪ ፈረስ አንድ አቅጣጭ ብቻ እንዲያይ የተገደበ በመሆኑ ነው እንጂ ይህንን እንደማስረጃ አድርጎ ያቀረበው፤ ነገሮችን ሰፋ አድርጎ የመመልከት አድማስ ቢኖረው ኖሮ፤ የጠቀሳቸውን ሦስት ትግርኛ ተናጋሪዎች ታሪክ ተመልክቶ፤ እነሱ ይሆኑ ተስፋዬ ደበሳይ ትግርኛ ተናጋሪ በመሆኑ ሊቀርቡት የሞከሩት ወይስ እርሱ? ብሎ ነገሮቹን ከተለያየ አቅጣጫ በገመገመ ነበር።

ገብረ ሥላሴ ዘድንግል በ1969 ዓም መጀመሪያ ላይ በሞት በመለየቱ፤ ሰፋ ያለ ጊዜ በዓብዮቱ ዓመታት ውስጥ ስላላሳለፈ የፖለቲካ አመለካከቱ ግልጽ ሆኖ ያልታየ ሰው ነበርና፤ እንደ ተስፋዬ ርስቴ ባልተጨበጠ ማስረጃ ሰውን መወንጀል ስለማልፈቅድ አልፈዋለሁ። መሰለ ሐጎስና ኪዳኔ ተስፋዬ ግን፤ ሁለቱም የለየላቸው የወያኔና የሻዕብያ አባላትና ደጋፊዎች መሆናቸውን፤ መሰለ ሐጎስ ገና የመቶ አለቃ እንደሆነ ከሕወሃት ጋር በመቀላቀል፤ ኪዳኔ ተስፋዬ ደግሞ ገና ምክትል የመቶ አለቃ ሆኖ ኤርትራ ክፍለ ሃገር ከተመደበበት ጊዜ ጀምሮ ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ያለውን ጥላቻ በግልጽ ሲያኪያሂድ የነበረና የሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑ ከገዛ ኮርስ ጓደኞቹ ጋር እንኳን የማይቀየጥ እንደነበረ የታወቀ ሲሆን፤ በመጨረሻም ኤርትራ ስትገነጠል በኤርትራዊነቱ አምኖ ኢትዮጵያን ትቶ የሄደ ሰው ነው። ታዲያ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ እነዚህን ሁኔታዎች አላውቅም ነው የሚለው ወይንስ እነዚህን ሁኔታዎች የሚያውቁት ወይ ሞተዋል ወይም በሃገር የሉም ብሎ ይሆን፤ የእነ ኪዳኔንና የእነ መሰለ ሐጎስን ዘረኝነት በተስፋዬ ደበሳይ ላይ ለመለጠፍ የሞከረው? ምክንያቱን የሚያውቀው ራሱ ተስፋዬ ስለሆነ ጉዳዩን ለራሱ እተወዋለሁ። ዶክተር ተስፋዬ ግን ኢትዮጵያ ብሎ የታገለ እንጂ በጠባቡ እንደነ መሰለና ኪዳኔ ትግራይና ኤርትራ ብሎ የታገለ አልነበረም።

## የተስፋዬ ርስቴ ጀግኖችና ምስክሮች

ተኮላ ማሞ

ተስፋዬ ርስቴ በተደጋጋሚ እንደ ጀግና በመጽሐፉ ላይ የሚጠቅሰው፣ እንደማጣቀሻም የሚጠቀምበትና የተለያዩ ቅጽሎች ከስሙ ፊት በማስገባት ‘ታዋቂውና አስጨናቂው’ መርማሪ እያለ የሚያሞካሸው ተኮላ ማሞ ማን እንደሆነ ከ1969 ዓም ጀምሮ በደርግ የምርመራ ክፍል ውስጥ ያለፉ ሁሉ የሚያውቁት ነው። ተኮላ የደርግ መርማሪ ሲሆን እንደሠለጠነ መርማሪ እስረኞችን በጥያቄ በማውጣጣትና በሚናገሩት ነገሮች መካከል የሚቃረኑና የሚጣረሱ ሁኔታዎች ቢኖሩ በዚያ ውስጥ ገብቶ ነገሮችን ፈልፍሎ የሚያወጣ መርማሪ ሳይሆን፣ እስረኞችን ገና ከእስር ክፍል ወደ ምርመራ ክፍል ከሚወስድበት ጊዜ ጀምሮ ሴት፣ ወንድ፣ ሽማግሌ ሳይል፣ በእርግጫ፣ በጥፊ፣ ቀደም ሲልም ተገርፈው ለድጋሚ ጥያቄ የሚወሰዱ ከሆኑ ቁስላቸው ላይ በጫማው በመቆም የሚያሰቃይ፣ ሰብዓዊ ርህራሄ የሌለው አውሬ ነበር። በተለይ ሴቶች ተመርማሪዎችን የሚሳደበው ስድብና ማስፈራራት ኢትዮጵያውያን እንደዚህ ዓይነት ብልግናና ጭካኔ አለን ወይ ብሎ የሚያስገርም ነበር። ምርመራ ክፍል ከወሰደም በኋላ አንዳንዶቹን ለግርፊያ እንደዘቀዘቃቸው ትቷቸው ለምሳው ይሄድ የነበረ አረመኔ ነበር። በዕርግጥ እንደነተስፋዬ ርስቴ ዓይነቶቹ ተምረናል የሚሉ የምሁር ደንቆሮ መኮንንኖች እንኳንስ ያኔ በገነኑበት ዘመን ይቅርና፣ አሁንም የሚከራከሩት ተሰቃዩ፣ ተገረፉ የሚባሉት ሁሉ የኢሕአፓ አባላት ስለሆኑ ቢገረፉ፣ ቢቆረጡ፣ እንደዶሮ ተዘቅዝቀው ምርመራ ክፍል ውስጥ ተትተው ቢቆዩ ምን አለበት ብለው ነው።

ሻምበል ተስፋዬ! ሌላው ከዚያ በኋላ ተምሬ ተመርቄበታለሁ የምትለው የሕግ ትምህርት ቀርቶ በአባ ዲና ፖሊስ ኮሌጅ የተማርከው መሠረታዊው የሕግና የወንጀል ምርመራ ትምህርት እንኳን ለአንድ መርማሪ ‘አስጨናቂ፣ ታዋቂ’ የመሳሰሉትን ቅጽሎች የሚያሰጡት በተማረው የፖሊስ የአጠያየቅ ዘዴና ቴክኒክ የተደበቁ ሚስጥሮችን ፈልፍሎ ሲያወጣ እንጂ፣ ስንቱን ንጹህ ዜጋ ገና ለገና የኢሕአፓ አባል ሳይሆን አይቀርም ብሎ እንደ ዶሮ ዘቅዝቆ ሰቅሎ፣ በአጠና በመቀጥቀጥ ያላደረገውን ድርጊት አድርጌያለሁ ብሎ እንዲፈርም በማስደረግና ያለወንጀሉ የዕምነት ቃሉን ሰጥቷል ብሎ በማሰር ወይም በመግደል አለመሆኑን ለመገንዘብ ይረዳህ ነበር።

ፈቃዱ አስቻለው

ይህኛውም የተስፋዬ ርስቴ ጀግና እንደተኮላ ሁሉ፣ በኢሕአፓ አባልነት የተጠረጠሩ ወጣቶችን በማሰቃየትና በመቀጥቀጥ የታወቀ ሲሆን፣ በተለይም የሚታወቀው በሴት ተጠርጣሪዎች ብልት ውስጥ እንጨት በመጨመር በመመርመርና አንዳንዴም በግድ በመድፈር ነበር። እንዲያውም የሚያደርገው ድርጊት በደርግ ደረጃ እንኳን ከመጠን በማለፉ በአንድ ወቅት ታስሮ እንደነበር የሚታወቅ ነው።

ፈቃዱ አስቻለው፣ በተስፋዬ መጽሐፍ ላይ በተለይ በገጽ 103-104 ላይ እንዴት የኢሕአፓ አባላት በሞተር ሳይክል ሲጓዝ ሊገድሉት እንደሞከሩና ከሞተር

ሳይክሉ ላይ ዘልሎ በመውደቅ በፍጥነት ተገለባብጦ ካመለጠ በኋላ ሦስቱንም በኮልት ሽጉጥ እንደለቀማቸው ከራሱ አንደበት ተጠቅሶ ተጽፏል። መቼም ፈቃዱን በቅርብ የሚያውቁት ሰዎች የቱን ያህል ወሬ እንደሚያጋንን ያውቁታልና አይደንቃቸው ይሆናል። በወቅቱ የተፈጸመው ግን የሚያሳዝን ሁኔታ ነበር። ፈቃዱ ላይ ባለው ዕለት ተተኩሶበት ነበር። በተኩሱ ስለተደናገጠ ከሞተር ሳይክሉ ላይ፣ እሱ አሁን ለወሬ አሳምሮ እንዳቀረበው ዘልሎ ሳይሆን፣ በድንጋጤ ወደቀ። የተኮሱበት ሰዎች የሞተ መስሏቸው አመለጡ። ፈቃዱ አድፍጦ ተኝቶ ቆይቶ ሲያበቃ በአካባቢው የነበሩ የዓብዮት ጠባቂዎችና ነዋሪዎች ሁኔታውን ለማየት ከተሰባሰቡ በኋላ፣ ሁኔታው መረጋጋቱን አይቶ ከተኛበት ከተነሳ በኋላ ነበር፣ ወሬ ለማየት መጥቶ ተሰብስቦ ከነበረው ሕዝብ መካከል ቆመው የነበሩ ሦስት ንጹህ ወጣቶችን የገደለው። አሁን ግን ጊዜው ስለዘገየና ሁኔታዎች የተዘነጉ ስለመሰለው ራሱን ልክ እንደ ፊልም አክተር አድርጎ *'ከሞተር ሳይክሉ ዘልዬ በመውደቅ በፍጥነት ተገለባብጬ ካመለጥኩ በኋላ ሦስቱንም በኮልት ሽጉጥ ለቀምኳቸው' (ገጽ 103-104)* ብሎ ታሪኩን የሚያወራውና ሻ/ል ተስፋዬም ተቀብሎ የሚያራግብለት። ይህ ነፍሰ ገዳይና በአሁኑ ጊዜ የመጽሀፍ ቅዱስ ተከታይ ሆንኩ ባይ ነው አንዱ የተስፋዬ የታሪክ ምሥክር።

<u>'ዛሬም እንደያን ጊዜው ነው የሚያስቡት'</u>

ተስፋዬ በመጽሐፉ መግቢያ ገጽ IV ላይ *'ስለ መጽሐፉ የደርግ የኢሕአፓና የመኢሶን አመለካከት ደጋፊ ናቸው ያልኳቸውን በጣም ጥቂት ሰዎች አስነብቤ ሃሳባቸውን ለማግኘት ሞክሬያለሁ። (የሚገርመው ግን እነዚህ ሰዎች ሁሉም ዛሬም እንደያን ጊዜው ነው የሚያስቡት።)'* የሚል አስተያየት አስፍሯል።

በውል ምን ለማለት እንደፈለገ የሚያውቀው እርሱ ራሱ ብቻ እንጂ፣ ለአንባቢ ግን አሻሚ መልዕክት ነው። ቢሆንም እንዲረዳው የሚያስፈልገው ነጥብ ቢኖር በተለይ ሕዝባዊ መንግሥት ብሎ የተነሳው ቡድን አሁንም ቢሆን ጥያቄው ያው ነው። ሻ/ል እና መሰሎችህ በንጉሡ ዘመን 'ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለዘለዓለም ይኑሩ' በደርጉ ጊዜ 'ከቆራጡና ከዓብዮታዊው መሪያችን አመራር ጋር ወደፊት' ስትሉ ኖራችሁ፣ አሁን ወያኔ ሥልጣን ሲቆናጠጥ ደግሞ ስለኢትዮጵያ ሲሉ ሲታገሉ የነበሩ ታጋዮችንና ድርጅት ስም እያጎደፋችሁ ለወያኔ እጅ መንሻ ጽሑፍ ማቅረብ ሙያ ቢመስላችሁም፣ ቆራጥ አቋም ያላቸው ግን ዓላማቸው ምንጊዜም አይለወጥም። ዛሬም ሕዝባዊ መንግሥት እንጂ ሌላ ጥያቄ አናነሳም። ለመጣው ሁሉ እያጎበደዱና፣ ከሁሉም ጋር እየተሞዳሞዱ ቆራጥ ኢትዮጵያውያንን ለወያኔ በእጅ መንሻነትን እያቀረቡ ማስወጋቱንና መገለባበጡን ለነ ሻ/ል ተስፋዬ እንተውላቸዋለን።

<u>*ማጋነን*</u>

ሻ/ል ተስፋዬ በተለይ ከቀድሞው አለቆቹና የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በከርቸሌ ቆይታው ወቅት ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንዴት ከከርቸሌ እንዳስወጣውና፣ እዚያስ በነበረበት ጊዜ ድንገት ቢያዝበት ለማጥፋት ሲል እንዴት ጽሁፉን በቀለም ይጽፍ እንደነበረና፣ ሁልጊዜ ውሃ ይዞ በመተኛት ቢደረስበት ሊያፈስበትና ሊደመስሰው ዝግጁ እንደነበረና ጽሑፉን ለማውጣት ሌሎች ዘዴዎችንም እንደተጠቀመ ገልጿል። እነዚህን ክፍሎች ለማጣፈጥ ካላቀረባቸው በስተቀር የኢትዮጵያ ሕዝብስ ሆነ ወያኔ ስለደርግ አባላት የአስራ ሰባት ዓመታት ድርጊት ምን የማያውቀው ሚስጥር አለና ነው፣ ልክ ታላቅ የስለላ ሰነድ የሚያስወጣ ሰላይ ይመስል ያንን ሁሉ ማጋነን የፈለገው። ምናልባት የሚያደንቃቸው መርማሪዎች እነተኮላ ቆራጥ የሆኑት የኢሕአፓ አባላት ምስጢር ላለማውጣት ሲሉ እንዴት ራሳቸውን የሚያጠፉበት ሳያናይድ ታብሌት ይውጡ እንደነበር የነገሩትን ሲሰማ እሱም ወግ እንዳይቀርበት ብሎ የጨመረው ይሆናል።

እንኳንስ ከርቸሌ ውስጥ ታጉራችሁ በወያኔ ቁጥጥር ስር ውላችሁ ቀርቶ፣ ከመታሰራችሁ በፊት እንኳን እወያኔ እጅ ይገባ ይሆናል ብላችሁ አስባችሁ አንዲት ሰነድ እንኳን ከደህንነቱ መሥሪያ ቤት ሳታጠፉ፣ የሃገሪቱን የሚስጥር ሰነድ አሳልፋችሁ የሰጣችሁ የመረጃ ሠራተኛ ተብዬዎች፣ እስር ቤት ውስጥ ያገኘሁትን መረጃ ለማውጣት ይህንን አደረግሁ፣ ይህንን ፈጠርኩ የሚለውን ታሪክ የሚሰማ ሕዝብ የሚታዘባችሁ ይመስለኛል። የእራሳችሁን ጉድ እንኳን ለመሸፈን ሞራል አጥታችሁ እርስ በእርሳችሁ የምትወነጃጀሉ ቡድኖች ሌሎችን ለመውቀስም ሆነ ለመተቸት የሞራል ብቃቱም የላችሁና፣ ፍርዱንና ትችቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትቶ ታሪኩን እንዳለ ማስቀመጡ ይመረጥ ነበር።

## <u>መሞጋገስ</u>

ሻ/ል ተስፋዬ፣ አለቃውን፣ የደህንነት ሚኒስትሩን በተመለከተ '731 እስረኞች በአንድ ጊዜ በምህረት ከእስር እንዲፈቱ ለተደረገው ውሳኔ የደህንነቱ ሚኒስትር ቀዳሚውና መሪው አንቀሳቃሽ እንደነበሩ ጸሐፊው ምስክር ነው" (119) በማለት ያሞካሻቸዋል። ምንም ጥፋት የሌለባቸውን በሺሆች የሚቆጠሩ ሰዎችን አጉሮ የያዘ መንግሥት የደህንነት ሚኒስትር፣ 731 ሰዎችን አስፈታ ተብሎ ከማወደስ ይልቅ፣ ስንቶቹን በግፍ እንዳስገደለ መናገሩ ምሥክርነት በሆነ ነበር። በ1969 ዓም እና በ1970 ዓም ውስጥ የደህንነት ሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ገና አጠቃላይ የመረጃ ማመዛዛኛና ማከፋፈያ ኮሚቴ ተብሎ በሚታወቅበት ዘመን፣ ስንት ዜጎች በጸረ ዓብዮተኛነት ስም በማዕከላዊ ምርመራ በኩል ቃላቸውን ብቻ ከሰጡ በኋላ፣ ራሳቸውን በሕግ የመከላከል ዕድል እንኳን ሳይሰጣቸው፣ የስም ዝርዝራቸው በሰንጠረዥ ከወጣ በኋላ በወቅቱ የኮሚቴው ኃላፊ፣ ማለትም አንተ በምታወድሳቸው የደህንነት ሚኒስትር ከዚህ ተራ ቁጥር እስከዚህ ተራ ቁጥር ያሉት አደገኞች ስለሆኑ አብዮታዊ እርምጃ ቢወሰድባቸው፣ ከዚህ ቁጥር እስከዚህ ያሉት ደግሞ ታስረው ቢቆዩና ከዚያ በታች ያሉት ግን ቢፈቱ የሚል የውሳኔ ኃሳብ ለደርግ እየቀረበ፣ አንተ እንደ ጀግንነት በገለጽከው ዓይነት አገዳደል

'እንደ ዶሮ አንገታቸው ተቆልምሞ' እንደሞቱ እየታወቀ አለቃውን እስረኞች በማስፈታት ቀዳሚውና መሪው አንቀሳቃሽ ነበሩ ሲል ያወድሳል።

ደራሲው ብቻ ሳይሆን የአነጋገራቸው የደርግ አባላትም ጭምር፣ በተለይ የኢሕአፓ አባላት ናቸው ብለው በገደሏቸው ዜጎች ሞት ምንም ዓይነት መጸጸት አያሳዩም። ለምሳሌ ያህል ካሳዬ አራጋው በገጽ 60 ላይ በሰጠው አስተያየት፣ 'በኢህሕአፓ እና በሌሎች የተፈጸመው ግድያ መጠን ማለፉን ባምንም ራሳቸው የፈጠሩት ስለሆነ አላዝንም። የ *60* ዎቹ ባለሥልጣናት ግድያ ግን ምን ጊዜም ይጸጽተኛል' ብሏል። እንዲህ ዓይነቱን አገም ጠቀም አነጋገር ምን አመጣው? በአንድ በኩል ግድያው ከመጠን እንዳለፈ መናዘዝ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ያለመጸጸት።

<u>ማጠቃለያ</u>

- የተስፋዬ ርስቱን መጽሐፍ እንዳነበብኩት በአጠቃላይ ሚዛናዊነት የጎደለውና አድሎአዊ ነው። በዕርግጥ ያነጋገራቸውም ሆኑ የጠየቃቸው ሰዎች በአንድ ወቅት ባለሥልጣናት የነበሩና በሥልጣን ዘመናቸው በፈጸሙት ወንጀል ለፍርድ የቀረቡ በመሆናቸው፣ እንደማንኛውም ተከሳሽ ራሳቸውን ከተከሰሱበት ወንጀል ነጻ ለማድረግ መከራከራቸውና ራሳቸውን መከላከላቸው ስለማይቀር ለምን የተከሰሱበትን ወንጀል ሁሉ አምነው የመጨረሻውን ከፍተኛ ቅጣት አልተቀበሉም ብሎ ማለት የዋህነት ነው። ማንም ቢሆን ቅጣቱን ለማቅለል መታገሉና መከላከሉ ስለማይቀር፣ የተስፋዬ መጽሐፍ ርዕስ 'ምስክርነት' መሆኑ ቀርቶ 'የመከላከያ ምሥክርነት' ቢባል የሚስማማው ርዕስ ይሆን ነበር።
- ሌላው በግልጽ የሚታየው ነጥብ፣ ባለታሪኮቹም ሆኑ ደራሲው በሙሉ የጊዜውን አዝማሚያ ተከትለው፣ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት የልብ ትርታ እያዳመጡ የሚያስደስተውን መልስ የሚሰጡ ነው የሚመስሉት። በወቅቱ ያለው መንግሥት በኢሕአፓ ላይ የቱን ያህል የገዘፈ ጥላቻ እንዳለውና ዘመቻም በማካሄድ ላይ መሆኑን በማወቅ ይመስላል አንዱ 'በኮልት ለቀምኳቸው' ሌላው ደግሞ 'በኢሕአፓ ላይ በተፈጸመው ግድያ አላዝንም' የመሳሰለ አስተያየት መስጠት ድረስ የደፈሩት።
- ሻ/ል ተስፋዬ በሁለተኛው ዕትም መግቢያ ላይ ስለመጽሐፉ ስለተሰጡት አስተያየቶች ሲገልጽ "የወያኔ ቡችላ"፣ "የኢሕአዴግ መልዕክተኛ"፣ "አድላዊ" ነህ ተብያለሁ ሲል ጠቅሷል። ተስፋዬ ምንም እንኳን በደህንነቱ መሥሪያ ቤት ቢሠራም በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ባለው ግርዶሽ (Compartmentation) የተነሳ ሁሉንም እንቅስቃሴ ላያውቅ እንደሚችል አስቀምጦታል። ያላወቀውንና ያልሰማውን ደግሞ ለምን አልጻፍክም ተብሎ ሊታማ አይገባውም። ግን አንድ መሠረታዊ የሆነ የኢንተለጀንስ አሠራር በመዘንጋቱ ላስታውሰው እወዳለሁ። አንድ ሰው የአንድ ሥርዓት

ወይም ቡድን መልዕክተኛ ወይም 'ቡችላ' (ይህንን ቃል እንኳን እራሱ ስለተጠቀመበት አነሳሁት እንጂ ልጠቀምበት አልፈልግም ነበር)፣ የሚሆነው ዘወትር በፈቃደኝነት ወይም አውቆት ላይሆን ይችላል። ብዙ ሰዎች ሳያውቁት፣ ከየዋህነት፣ የሌላ ቡድን ዓላማ አራማጅ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። በተለይም በዕፅ ንግድ ላይ የሰው መልዕክት በሻንጣው ውስጥ ምን እንዳለ ሳያውቁ ተቀብለው ለተላከለት ሰው የሚያደርሱ የዋህ አቀባባዮች (Mule) ተብለው እንደሚታወቁት ሁሉ፣ ተስፋዬም አውቆም ይሁን ሳያውቅ ይህንን መጽሐፍ በማውጣት፣ ዘመቻ በኢሕአፓ ላይ በማካሄድ ለወያኔ ከፍተኛ አገልግሎት እንዳበረከተ መገንዘብ ካልቻለ፣ ሊታዘንለት የሚገባ ሰው ነው።፡ እንዲያውም መጽሐፉን ከአዲስ አበባ ያመጣልኝ ሰው "ይቺ ፖሊስ ደህና መጠሪያዋን ከወያኔ አገኘች" ብሎ ነው የሰጠኝ። አባባሉ አሁን ወያኔ በያዘው ተቃዋሚ ድርጅቶችን የማውገዝ ዘመቻ ኢሕአፓን የሚያጥላላ ዘመቻ ከወያኔ በበለጠዬ በማካሄዱ ባለውለታው በመሆኑ ነው።

- ሻ/ል ተስፋዬ ራሱም የወንጀሉ ተሳታፊ ሆኖ ራሱን ለመከላከል ካልፈለገ በስተቀር፣ የዚህ ዓይነቱን ብዙ የደርግ ባለሥልጣናትና መርማሪዎች በአንድነት ተከማችተው የማነጋገር ዕድል ሲያገኝ፣ በተለይ እነደነ ተኮላ ዓይነቱን መርማሪዎች፣ ለመናገር ፈቃደኛ ከሆኑ ማን ማንን በግፍ እንደገደሉ፣ ምርመራ ላይ ይሞቱና ይገደሉ የነበሩ ወጣቶች የት እንደተጣሉ? ምንም ዓይነት ፖለቲካ ውስጥ ሳይገቡ በስሕተትና በጥርጣሬ ተይዘው ከተገረፉ በኋላ ቢፈቱ የደርግ የምርመራ ክፍልን አሠራር ያጋልጥ ይሆናል ተብሎ ተፈርቶ የተገደሉ እነማን እንደሆኑ? ባሳለፉት የምርመራ ወቅት የሚጸጽታቸው ነገር ቢኖር እንዲናገሩ ቢያደርጋቸው ኖሮ ዕውነትም መጽሐፉ ምሥክርነት በሆነ ነበር።

- በመጨረሻ ላይ መግለጽ የምወደው በአለፉት ሰላሳና አርባ ዓመታት በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ አልፈናል፣ እርስ በርሳችን ተዋግተናል፣ ተጋድለናል፣ ተገነጣጥለናል፣ ተወነጃጅለናል ብቻ ምን ያልተደራረግነው ነገር አለ? ግን ያም ሁሉ ሆኖ አልበቃን ብሎ አሁንም አዲስ መቋሰል ይዘናል። ረጋ ብለን ራሳችንንና ድርጊታችንን መለስ ብለን የመመርመሪያ ጊዜ ወስደን ምን ነበር ያጠፋነው? የት ቦታ ላይ ነበር የተሳሳትነው? ብሎ ራሳችንን መጠየቅና ስሕተታችንን መቀበል ውርደት መስሎን አሁንም ስሕተታችንን ትክክል ነው ብለን ለማሳመን እንገታገታለን። ጥፋትን አምኖ መቀበልና ለዕርማት መዘጋጀት የትልቅነትና የጨዋነት ምልክት ነው። ግን ነፍሰ ገዳዮች፣ አካል አጉዳዮች፣ ሃገር ገንጣዮች ሳይቀሩ እየተነሱ ወንጀላቸው እንደ ጀግንነት የሚወደስላቸውና እነሱም የሚፎክሩ ከሆነ ሕሊናና ጨዋነት የጎደለን ይመስለኛል። የፈረስ ልጅ ሆነን ስለጥፋታችን ደንገጥ ብሎ መታረም እንጂ የስንቶችን ሕይወት ቀጥፎና አካል አጉድሎ የተሰዉ ወገኖችን ስም ማጥፋትና ጀብዱ እንደተፈጸመ ሁሉ መፎከርና መወዳደስ እንደ የአህያ ልጅ ሆኖ ጥሎ እንደመራገጥ ነው የሚቆጠረው።